ለገነት ግርማ ማስታወሻ

አባትና እናትሽ ገነት ብለው ጠሩሽ
ምንኛ ደስ ባለኝ እንከንየለሽ ቢሉሽ።

ለትምህርት ብለሽ፤ ብትወጪ ካገርሽ
የወገን ሰቆቃ፤ ከልብ አልወጣ ቢልሽ
የእህቶችሽ ውርደት፤ የእግር እሳት ሆኖብሽ
የወንዶች ትምክህት፤ አላስተኛ ብሎሽ
ቆርጠሽ ትግል ገባሽ፤ ምቾትሽን ጥለሽ።

ለዓለም ስታስተጋቢ፤ የሴቶችን ብሶት
በአውሮፓ በእስያ፤ ቆመሽ  ለእኩልነት
ለድምፅ አልባዎቹ፤ ስታሰሚ ጩኸት
ፍትህ ስትጠይቂ፤ ስትደክሚ ስትልፊ
ቃልሽን ጠብቀሽ፤ ቃልኪዳን ሳታጥፊ
ቆራጥነትሽን፤ ሳታሽራርፊ
ወንድ ሴት ሳይባል፤ ሲመሰክሩልሽ
የአይን ምስክር ነኝ፤ በትህትናሽ
ለትልቅ ትንሹ፤ ያለሽን አክብሮትሽ
ለለፋሽው ድካም፤ ወሮታ ሳያሻሽ
ክብርን ተጎናጽፎሽ፤ በእህት ወንድሞችሽ
እንኳን ለዚህ አበቃሽ፤ የኛ እንከንየለሽ።

ኩራት ለኢህአፓ፤ ኩራት ለጓዶችሽ
ለኢትዮጵያውያን ሴቶች፤ አኩሪ ጌጣቸው ነሽ
ለኛም ለወንዶቹ፤ መመኪያ ኩራት ነሽ
ሁሌም አርአያ ነሽ፤ በተምሳሌነትሽ
ማጋነን አይመስልም፤እንከንየለሽ ብልሽ።

ከጎላ ምንጭ